## አንቀጽ 5

## የስራ አመራር ቦርድ የስብሰባ እና የድምፅ አሰጣጥ ስነ-ስርዓት

1. ቦርዱ በሶስት ወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማናቸውም ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል፤
2. አስቸኳይ ስብሰባ በቦርድ ሰብሳቢ ወይም በኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር ሊጠራ ይችላል፤
3. ከቦርድ አባላት ውስጥ ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፤
4. ቦርዱ ውሳኔ የሚያሳልፈው በድምጽ ብልጫ ይሆናል፤ ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፤
5. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቀ ሆኖ ቦርድ የራሱን የስብሰባ ስነ-ስርዓት መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

## ክፍል ሦስት

## አንቀጽ 6

## የቦርድ ስብሰባና ክፍያን በተመለከተ

የቦርድ አባላት በሙሉ በመደበኛ ወይንም በአስቸኳይ በሚሰበሰቡበት ጊዜ

1. ለቦርድ ሰብሳቢ-----------------------------500(አምስት መቶ ብር)
2. ለቦርድ ፀሐፊና አባላት----------------------450(አራት መቶ ሀምሳ ብር)
3. ለሌሎች ስብሰባዉን ለሚያስተባብሩ (የኤጀንሲው ምክትል ዳይሬክተር፤ ከሁለት ያልበለጡ አስረጂዎች፤ እና ቃሌ- ጉባዔ ያዥ(1))------300(ሶስት መቶ ብር) ክፍያ በቀን ይከፋላቸዋል።

## አንቀጽ 8

## የቦርድ ውሳኔ ተፈፃሚነት

1. በዚህ መመሪያ መሠረት የቦርድ ውሳኔ ካልተለወጠ ወይም ካልተሻሻለ ወይም ካልተሻረ በስተቀር በተቋሙ ዋና ዳይሬክተር አማካኝነት ተፈፃሚ ይሆናል፤
2. ቦርዱ ውሳኔ በወሰነው መሠረት የመፈፀም ወይም የማስፈፀም የተቋሙ ዋና ዳሬክተሩ ግዴታና ኃላፊነት ነው፤
3. የቦርዱ ውሳኔ በውሳኔው መሠረት መፈፀሙን ቦርዱ ይቆጣጠራል፤ ያረጋግጣል፤ አስፈላጊውን ትዕዛዝ ይሰጣል።

## አንቀጽ 10

## ስለ ቦርዱ ቃለ-ጉባኤ ቅርጽ

የቦርዱ ቃለ-ጉባኤ ቢያንስ የሚከተለውን ቅርፅ ይይዛል።

1. የቦርድ ቃለ-ጉባኤ መሆኑን የሚያሳይ የተቋሙንና የቦርዱን ሙሉ ይፋዊ ስብሰባው የተደረገበት በታ፤ ቀን፤ ወር እና ዓመተ-ምህረት እንዲሁም ስብሰባው የተጀመረበትና የተጠናቀቀበትን ሰዓት፤
2. በስብሰባው ላይ የተገኙት የቦርድ አባላት ሙሉ ስምና የስራ ኃላፊነት ፤
3. የቦርዱ ፀሐፊ ወይንም የዕለቱ ፀሐፊ ሙሉ ስም፤